## ምን ማምጣት ያስፈልጋል

**የቻሉትን ያህል ብዙ ሰነዶችን ይዘው ይምጡ፡**

- የቪዛ ሰነዶችን
- የመታወቂያ ሰነዶችን
- የባንክ ስቴትመንት (ለፋርማሲ ድጋፍ የሚያስፈልግዎት ከሆነ)
- የህክምና ሰነዶችን

## ሌሎች ነጻ የጤና አገልግሎቶች

**በቪክቶሪያ መንግስት መመሪያ መሰረት፣ ሁሉም በቪክቶሪያ ውስጥ ጥገኝነት የሚጠይቁ ሰዎች ሜዲኬር ባይኖራቸውም ነፃ የህዝብ ጤና አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው።**

የህዝብ ጤና አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራል፡

- የህዝብ ሆስፒታሎችን
- የአደጋ ጊዜ አገልግሎት ስጭ አምቡላንስ
- የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች
- የአእምሮ ጤና ድጋፍ ስጪ
- የጥርስ ህክምና አገልግሎቶች
- ሳይከተቡ የቀሩዋቸውን ክትባቶች ማግኘት

ማንኛውንም የደም (ፓቶሎጂ) ወይም የምስል (ኤክስረይ፣ አልትራሳውንድ ወዘተ) ምርመራ የሚያስፈልግዎ ከሆነ እባክዎን ይምጡ እና ያነጋግሩን።

ማግኘት የሚገባዎትን ነፃ የጤና አገልግሎት ለማግኘት የእኛ እርዳታ ሊያስፈልግዎት ይችላሉ። በሆስፒታል ወይም በሌላ የጤና አገልግሎት ውስጥ የጤና አገልግሎት እንዳያገኙ ከተከለከሉ ወይም ለተሰጠዎት አገልግሎት እንዲከፍሉ ከተደረገ እባክዎን ይምጡና ያነጋግሩት።



ASRC
LGBTQIA+
አካታች ነው

ASRC
Asylum Seeker Resource Centre

# የጤና ፕሮግራም

**ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ሐሙስ፣ እና ዓርብ**
**(ሮብ ዝግ ነው)**

10:30ኤም - 4:00ፒኤም

03 9274 9898
health@asrc.org.au

የትርጉም አገልግሎቶች ይገኛሉ




የአቦርጂናል እና የቶረስ ስትሬት ደሴት ህዝቦች የምንኖርበት፣ የምንማርበት እና የምንሰራበት መሬት ቀደምት ህዝቦች እና ባህላዊ ጠባቂዎች እንደሆኑ እውቅና እንሰጣለን። ለነሱ፣ ለልማዳቸው፣ ለባህላቸው እና ለቀደሙት እና በአሁኑ ጊዜ ላሉት ሽማግሌዎች ያለንን ክብር እንገልጻለን። የቀደምት ህዝቦችን ሉዓላዊነት እና መሬታቸው በፍፁም ለሌሎች ያልተሰጡ መሆኑን እናምናለን። ይህ መሬት ሁሌም የአቦርጂናል ህዝቦች ነበር ወደፊትም ይሆናል

# በጤና ክሊኒካችን የምናቀርባቸው አገልግሎቶች

**የጥርስ ሕክምና**

እንደአስፈላጊነቱ ወደ ሮያል የጥርስ ህክምና ሆስፒታል ወይም የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት ለተጨማሪ የጥርስ ህክምና ሊላኩ ይችላሉ።

**ስለ ጤና አጠባበቅ ትምህርት**

ሊደርሱ የሚችሉ የጤና ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችሉ ክህሎቶችን እና እውቀትን የሚሰጡ መደበኛ ፕሮግራሞች።

**የሕክምና ቀጠሮዎች**

በASRC ጤና ውስጥ ብዙ ቀናት ዶክተር አለ።
ሜዲኬር ከሌለዎት ቀጠሮ አስይዘው የASRC ጤናን ሐኪም ማግኘት ይችላሉ።
ሜዲኬር ካለዎት የማህበረሰብ ዶክተር ለማግኘት እኛ ልንረዳዎት እንችላልን።

**መድሃኒት ለመግዛት የወጡ ወጪዎች አገዛ**

የፋርማሲ ፕሮግራሙን ለመቀላቀል፣ ያሉበት የፋይናንስ ሁኔታ ይገመገማል።
ለዚህ ግምገማ የ3 ወራት የባንክ ስቴትመንት ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ በየ6ት ወሩ የባንክ ስቴትመንት ማቅረብ ያስፈልግዎታል።

**ክትባቶች**

ነርሶች የቀሩ እና ያልተሟሉ ክትባቶች ካሉዎት ይህንን ይሰጡዎታል።
ዓመታዊ የጉንፍን ክሊኒክ ይገኛል።*
*ቀጠሮ ማስያዝ ያስፈልጋል። ለበለጠ መረጃ ያነጋግሩን።

**የማዳመጥ (የመስማት) ምርመራ**

ተገቢ ወደሆነ የማዳመጥ (የመስማት) አገልግሎት ስጪ መላክ።

**የአእምሮ ጤና እና የአእምሮ ህክምና (ሳይካትሪ)**

ሜዲኬር ባይኖርዎትም የአእምሮ (ሳይካትሪስት) ሐኪም ማየት ይችላሉ። የእኛ ዶክተሮች የሪፈራል ደብዳቤ ሊጽፉልዎት ይችላል።

**የነርሲንግ እንክብካቤ**

ነርሶች በየቀኑ ይገኛሉ። ከASRC ዶክተሮች ጋር ቀጠሮ ለመያዝ ልናግዝዎ ወይም ወደ ሌሎች የጤና እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሰጭዎች ልንልክዎ እንችላለን።

**የዓይን እንክብካቤ**

ወርሃዊ የአይን ክሊኒካችን ይሰራል። አስፈላጊ ከሆነ ወደ ሮያል ኦፕቶሜትሪ ኮሌጅ ልንልክዎ እንችላለን። ለመነጽር፣ ሌንሶች እና ክፈፎችም ላወጡት ወጭ እስከ 50 ዶላር የሚደርሰውን እንሸፍናለን።

**የሴቶች ክሊኒክ**

የመራቢያ ጤናን ጨምሮ የሴቶች ጤናን በተመለከተ የምርመራ፣ መረጃ እና አገልግሎቶች እናቀርባለን።

## ሌሎች አገልግሎቶች

- **የእግር ጤና (ፖዲያትሪ)**
- **የፊዚዮቴራፒ እና ኦስቲዮፓቲ (አጥንት፣ ጡንቻ፣ ነርቭ እና ቲሹ ህክምና)**
- **ደረቅ መርፌ (አኩፓንቸር)**
- **የአመጋገብ ባለሙያ (ዳይትሽያን)**
- **የስኳር በሽታ አስተማሪ**